# አሥራ አንደኛ ትምህርት ከመጋቢት 2 — 8 Mar 11—17

## መንፈስን ማሳዘንና መቃወም

**ሰንበት ከሰዓት**

ለዚህ ሳምንት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡ ሐዋ. 7:51፣ ዕብ. 10:24-25፣ ኤፌ. 4:25-5:2፣ 1ተሰ. 5:19-21፣ ማር. 3:28-29።

**የሳምንቱ ጥናት መሪ ጥቅስ፡- "ለቤዛ ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ አታሳዝኑ" (ኤፌ. 4:30)።**

መንፈስ ቅዱስ ኃጢአተኞች የሚገኙበትን ሁኔታ እንዲገነዘቡ የመምራት ልዩ ችሎታ አለው። እንዲሁም የሱስንና የእርሱን ይቅርታ የመቀበል ምኞት በውስጣችን እንዲነሳሳ ያደርጋል። መንፈስ ቅዱስ አሸናፊዎች የሚያደርገንንና ውብ የሆነውን የየሱስ ጸባይ ለማንጸባረቅ የሚያስችለንን ወደር የማይገኝለት ኃይል ይዞአል።

ደግሞም ይህን እጹብ ድንቅና ኃያል የሆነውን መንፈስ ቅዱስ--ደካማው ኃጢአተኛ ሊቃወመው ይችላል። መንፈስ ያለ ፈቃዳችን ሊያስገድደን አይችልም።

ኃጢአት እጅግ አድርጎ የማነሁለልና ስሜትን የመሳብ ተፈጥሮ አለው። ደግሞም--ይህ ተፈጥሮው አታላይና ወደ ሞት ጎዳና የሚመራ ነው። ኃጢአት እግዚአብሔርን፣ የእርሱን ቅድስናና በጎነት ሙሉ ለሙሉ ይቃረናል። ይህን መለኮታዊ ቅድስና የሚያንጸባርቀውና ማንኛውንም ከኃጢአት ጋር ተዛምዶ ያለውን ነገር የሚቃወመው መንፈስ ቅዱስ--ኃጢአት ስንሠራና ለመመለስ ፈቃደኞች ሳንሆን ስንቀር ያዝናል። መንፈስ ቅዱስ እጅግ ኃያል ቢሆንም ነገር ግን አዎንታዊ ተጽእኖው በውስጣችን ሊዳፈንም ሆነ በኃጢአተኛው ህይወት በመቀጠል ልንቃወመው እንችላለን። ወንጌል ይቅር የማይባል አንድ ብቻ ኃጢአት መኖሩን የሚነግረን ሲሆን ይኸውም መንፈስ ቅዱስን መሳደብ ነው (ማቴ. 12:31-32)።

በዚህ ሳምንት--መንፈስ ቅዱስን ማሳዘን፣ ማዳፈንና መቃወም የተሰኙትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ገጽታዎችን ይቅር ከማይባለው ኃጢአት ጋር እናጠናለን።

*እሑድ መጋቢት 3* *Mar 12*

### መንፈስ ቅዱስን መቃወም

በሐዋ. 7:51 ላይ የተሰጠን ማስጠንቀቂያ ምን ነበር? ማስጠንቀቂያው ለእኛም መሆን የሚችለው እንዴት ነው?

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

በመንፈስ ቅዱስ ላይ ኃጢአት መሥራት--በሚል የተገለጹ ኃጢአቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ተጠቅሰዋል። አብዛኞቹ እነዚህ ኃጢአቶች በግለሰብ ደረጃ ቢሠሩም ነገር ግን በሐዋ. 7:51 ከተጠቀሰው በመነሳት የቡድን ገጽታ ሊላበሱ እንደሚችሉ መገንዘብ እንችላለን። እስጢፋኖስ--የቀደሙት አመጻኞቹ እስራኤላውያን የወርቅ ጥጃ (ዘፀ. 33:3) ሠርተው ማምለካቸውን በማስታወስ የእርሱም ከሳሾች በተመሳሳይ አንገተ ደንዳኖች መሆናቸውን ሲነግራቸው እንመለከታለን። መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ነቢያት ተጠቅሞ የእነዚህን ሰዎች ልብ ለመንካት ቢመኝም እነርሱ ግን መልእክቱን ለማዳመጥ አሻፈረኝ በማለት መንፈስ ቅዱስን ተቃወሙ። ይህ እግዚአብሔርንና የእርሱን ዕቅድ የመቃወም አካሄድ በመጨረሻ አንዳንዶች የጌታ የሱስ ክርስቶስን ሥራዎች እንዲቃወሙ መንስኤ ሆኖአቸው ነበር። የሱስን በመከተል ሕያው ቃሉን በመታዘዝ ፋንታ አምልኮአቸው ውጪያዊውን ገጽታ የያዘ ሆነ።

በእግዚአብሔር የተፈጠረውና መተማመኑ ሁሉ በእርሱ ላይ የተመሰረተው ደካማው ሰብዓዊ ፍጡር የመንፈስ ቅዱስን ሥራ--ብሎም የእግዚአብሔርን ጸጋ መቃወሙ አስገራሚ ነው። መንፈስ ቅዱስ እንደ እግዚአብሔር ሁሉ ኃያል ቢሆንም ነገር ግን በግል ምርጫችን ጣልቃ ገብቶ አያስገድደንም። ምርጫችንን ያከብራል።

እግዚአብሔር አስገድዶን እንድናመልከው የሚፈልግ ቢሆን ኖሮ--የሰብዓዊውን ነጻ የመምረጥ ፈቃድ ጨፍልቆ በኤደን በአዳምና ሔዋን ላይ በመተግበር ዓለምን ከኃጢአት ቀውስ ለምን አላዳናትም ነበር? እግዚአብሔር--ሕይወት ወይም ሞት፣ መልካም ወይም ክፉ--ለመምረጥ የሚያስችለንን ነጻነት ሰጥቶ ፈጥሮናል። በዚህም እያንዳንዳችን እጅግ የተቀደሰና ከፍተኛ ዋጋ ያለው ስጦታ ተሰጥቶናል።

እያንዳንዱ ሰው ለሚሰጠው ውሳኔ ኃላፊነቱን በግሉ እንደሚወስድ ሁሉ--በተጨማሪ ሰዎች አንዱ ለሌላው ታማኝ እንዲሆኑ፣ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲታዘዙና ከየሱስ አጠገብ እንዳይርቁ (ዕብ. 10:24-25) የማበረታታት የጋራ ኃላፊነት አለብን። የእግዚአብሔርን ቃል ለመቀበል ስናንገራግርና የነቢያቱን መልእክቶች ሳንቀበል ስንቀር መንፈስ ቅዱስን እንቃወማለን።

ወደ ጥንቶቹ እስራኤላውን ስህተቶች መልከት በማድረግ በእነርሱ ላይ ፍርድ መስጠትና ትችት ማቅረብ ቀላል ነው። ነገር ግን የራሳችን ደካማ ምርጫዎችስ? የጥንቶቹ እስራኤላውያን ከሠሯቸው ስህተቶች በተመሳሳይ የእርስዎም የተሳሳተ ምርጫ ውጤት ፊት ለፊት ፈጥጦ ቢመለከቱት ምን ሊሰማዎ ይችላል?

ሌሎችን “በፍቅርና በመልካም ሥራ” ልንረዳ የምንችልባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው? እነዚህን እሴቶች በማጎልበቱ ረገድ የእርስዎ ኃላፊነት ምንድን ነው?

*ሰኞ መጋቢት 4* *Mar 13*

## *መንፈስ ቅዱስን ማሳዘን፡ ክፍል 1*

ይህን ጥቅስ ያንብቡ፡-- ኤፌ. 4:30። ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስን እንዳናሳዝን ያስጠነቅቀናል። ለመሆኑ መንፈስ ቅዱስን ማሳዘን ምን ማለት ነው?

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

መንፈስ ቅዱስ የመለኮት ኃይል ሳይሆን ነገር ግን የራሱ የሆነ ግላዊ ባህሪ ያለው ነው፡፡ ማዘን የሚችልበትም ምክንያት ይኸው ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስን የምናሳዝነው እንዴት ነው? ኃጢአትን መመልከት እንዲችሉ አድርጎ ዐይኖቻችንን መክፈት ከመንፈስ ቅዱስ ተግባራት አንዱ መሆኑን ማስታወስ ተገቢ ነው (ሐዋ. 16፡8)፡፡ መንፈስ ኃጢአታችንን ይቅር ወደሚለንና ወደሚቀድሰን የሱስ ይመራናል፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ--"ቅዱስ" በመባል ይታወቃል፡፡ የዚህ ትርጉም--ኃጢአትን መጥላቱን ያመለክታል፡፡ ነገር ግን በሁሉም ነገር ለእግዚአብሔር ታዛዦች በመሆን የምናስበውም ሆነ የምንናገረው ንጹህና ቅዱስ ሲሆን አብልጦ ደስ ይሰኛል፡፡ ይህ ማለት የቀረበልንን መለኮታዊ ጥሪ ከንቱ ከሚያደርግ ከማንኛውም ነገር ጋር ቁርኝት ስንፈጥር--በተቃራኒው ያዝናል፡፡ ማንኛውም ዓይነት ኃጢአትን በጉያ የመያዝ ወይም አሳሳቢውን የኃጢአት ጉዳይ ዝቅ አድርጎ የመመልከት አዝማሚያ እርሱን ያሳዝነዋል፡፡ መንፈስ ቅዱስን ማሳዘን እንደ ዋዛ መታየት የሌለበት ከባድ ጉዳይ ነው፡፡

ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስን ስለ ማሳዘን በኤፌ. 4፡30 ያቀረበው የመልእክት ዐውድ አንድ ሰው ክርስቶስን ተቀብሎ ከመለወጡ አስቀድሞ ይኖረው የነበረውን ሕይወትና ከተለወጠ በኋላ የሚመጣውን ማንነት ያመላክታል፡፡ በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት እንደ መሆናችን አንዱ ሌላውን ሊታገስ፣ ገራገርነቱን ሊያሳይ፣ ይቅር ሊል፣ ሊወድና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለንን ሕብረት ከሰላም ጋር አስተሳስረን ጠብቀን ልናቆይ ይገባል (ኤፌ. 4፡2-3)፡፡ አሁን በመንፈስ በመታደስ (ኤፌ. 4፡23) በአዲሱ አእምሮአችን የሱስን እየተከተልን (ኤፌ. 4፡17) በመሆኑ እንደ አሕዛብ በከንቱ አስተሳሰብ አንመራም (ኤፌ. 4፡17)፡፡ ይልቁንም እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕይወት እንኖራለን (ኤፌ. 4፡24-31)፡፡

በምዕራፍ 4 ከቀረቡት መሃል ማንኛውም ዓይነት አሉታዊ ክስተት በልባችን ቦታ እንዲኖረው ስንፈቅድና ከአንደበታችን በሚወጡ ቃላትም ሆነ በድርጊታችን ሲገለጥ--መንፈስ ያዝናል፡፡ መንፈስ ቅዱስን ማሳዘን ማለት በፈቃዳችን ኃጢአት መሥራታችንን በመቀጠል እኛን የሚቀድሰውንና ሕይወታችንን የሚቀይረውን የእርሱን መገኘት መቃወም ነው፡፡

መንፈስ ቅዱስ በእኛ የዕለት ከዕለት ህይወት ልቡ የማይነካና ግዴለሽ አይደለም፡፡ ኤፌ. 4፡25-31--ያንብቡና መንፈስ ቅዱስን የሚያሳዝኑትን ባህሪያት ዘርዝረው ያውጡ፡፡ መንፈስ ቅዱስ በእነዚህ ነገሮች የሚያዝነው ለምንድን ነው?

*ማክሰኞ* *መጋቢት 5* *Mar 14*

## *መንፈስ ቅዱስን ማሳዘን፡ ክፍል 2*

የመንፈስ ቅዱስ ማዘን መቻል እግዚአብሔር ማንኛውንም የምናደርገውን ነገር በግዴለሽነት እንደማይመለከትና ችላ ብሎ እንደማያልፍ ያሳየናል፡፡ ከአምላካዊው ፈቃድ ያፈነገጠ ውሳኔአችንም ሆነ የኑሮ ዘይቤያችን እግዚአብሔርን ይጎዳዋል፡፡

ጥቅሶቹን ያንብቡ፡--ኤፌ. 4፡25-5፡2፡፡ በመልእክቶቹ ምን ተነግሮናል? እነዚህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትእዛዛት ብንከተል ሕይወታችን አሁን ካለው ምን ያህል የተለየ ሊሆን ይችል ነበር?

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

እውነትን በፍቅር ስንናገር፣ በኃጢአት ስንቆጣ (ወደ ኃጢአት ያላዘነበለ ቁጣ)፣ ሠርተን ካገኘነው ከላባችን ፍሬ ለተቸገረው ስናካፍል፣ ንግግራችን ሌሎችን የሚያንጽና አምላካዊውን ጸጋ በአድማጮቻችን ልብ የሚያኖር ሲሆን፣ ደግ፣ ርኅሩኅና ይቅር ባዮች ስንሆን--መንፈስ ቅዱስን ደስ እናሰኛለን፡፡

በአፋችን ክርስቲያን መሆናችንን እየተናገርን ኑሮአችን ግን ክርስቶስ እንዳልመጣ የሚገልጽ፣ ሕይወታችን በአምላካዊው ምሪትም ሆነ ፍቅር ያልተነካ ዓይነት ከሆነ በእርግጥ መንፈስ ቅዱስን እናሳዝነለን፡፡ እውነትን እናምናለን እያልን ነገር ግን የየዕለት አኗኗራችን ከምንናገረው ጋር የሚቃረን ከሆነ አሁንም መንፈስ ቅዱስን እናሳዝናለን፡፡ ሐቀኝነት የጎደለውም ሥነ ምግባር እንዲሁ መንፈስ ቅዱስን ያሳዝናል፡፡ አምላካዊውን መልእክት ወደ ሌሎች የማድረስ ጥረታችን በሐቅ ላይ ከተመሰረተው ሥነ ምግባራዊ ባህሪ ጋር የተፋታ መሆን የለበትም፡፡ ኑሮአችን በተጨባጭ የእርሱ ታማኝ ልጆች መሆናችንንና ህይወታችን የሱስን የሚያንጸባርቅ ከሆነ በእግዚአብሔር ልብ ውስጥ ደስታ እናመጣለን፡፡

እነዚህ ጥቅሶች፡-- ኤፌ. 4፡3-4፣ 15-16፣ 32--በመንፈስ የመኖርን ኅብረት ገጽታ እንዴት ይገልጻሉ? በመንፈስ የተሞላ ሕይወት ከሌሎች አማኞች ተጓዳኝ ኅብረት ውስጥ ራሱን የሚገልጠው እንዴት ነው?

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

በኤፌ. ምዕ. 4 በዓይነቱ ለየት ያለ የአማኞች ኅብረት ገጽታ መስተዋሉ አስደሳችም አስገራሚም ነው፡፡ የመንፈሳዊው ኅብረት ጽንሰ ሃሳብ በብዙ ቦታዎች ተጠቅሶአል፡፡ የየዕለት ሕይወታችን በእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ የተመሰረተ እንደ መሆኑ "እርስ በርስ" (ኤፌ. 4፡32) ማለትም አንዱ ለሌላው በጎ በመሆን የመንፈስን ኅብረት ጠብቆ ማቆየት እንደሚገባ ጳውሎስ አጽንኦት ሰጥቶ ይናገራል፡፡ በቤተ ክርስቲያን "በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ" (ኤፌ. 4፡3) እየተጋን የእርስ በርስ ግንኙነታችንን ወደ ተሻለ ደረጃ ማሳደጋችን መንፈስን የማናሳዝንበት አበይት ክፍል ነው፡፡

እንደ መንፈስ ቅዱስ ማደሪያነታችን (1ቆሮ. 3፡16-17) የቤተ ክርስቲያናዊው የእርስ በርስ ግንኙነታችን ለእግዚአብሔር አብልጦ ትርጉም አለው፡፡ የክርስቶስ አካል እንደመሆናችን አንዱ ለሌላው ሊኖረው የሚገባ አስተሳሰብ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅድሚያ ይሰጠዋል፡፡

የሦስቱን መላእክት መልእክት እውነት (ራእ. 14፡6-12) ማወቅ መልካም ቢሆንም ነገር ግን ከሌሎች ጋር ያሎት ቀረቤታ ወይም አያያዝ ምን ይመስላል--በተለይ ከእርስዎ በታች ለሆኑ ወይም ለእርስዎ ምንም ሊያደርጉ በማይችሉ ላይ?

*ረቡዕ መጋቢት 6* *Mar 15*

## *መንፈስ ቅዱስን ማዳፈን*

ይህን ጥቅስ ያንብቡ፡-- 1ተሰ. 5፡19-20፡፡ *መንፈስ ቅዱስ ሊዳፈን የሚችለው እንዴት ነው?*

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

“ማዳፈን” የተሰኘው ቃል ከእሳት ጋር ተያያዥነት ያለውን ጽንሰ ሃሳብ ይዞአል። በ 1ተሰ. 5፡19 እና በኤፌ. 6፡16 የምናገኛቸው የእነዚህ የግሪክ ስርወ ቃላት መነሾ ተመሳሳይ ነው። የመንፈስ ቅዱስ እሳት መጥፋት እንደሚችል ከአባባሉ መረዳት ይቻላል። መንፈስ ቅዱስ ሁለት በጣም አስፈላጊ ነገሮችን እንደሚያደርግልን ማስታወስ የሚገባን ሲሆን ይኸውም--ኃጢአትን የምናስተውልበትን ዕውቀት መስጠትና ኃጢአትን የምናሸንፍበትን ኃይል ማጎናጸፍ ናቸው። እነዚህ ሁለቱም ከቅድስና ጋር ተያያዥነት አላቸው።

ጤናማ ሕይወት ለመኖር ማወቅ የሚያስፈልጉንን ነገሮች የእግዚአብሔር ቃል እና መንፈስ ቅዱስ ይነግሩናል። መንፈስ በእኛ ውስጥ ሲያድር የሚሰጠን ኃይል በአወቅነውና በተረዳነው መሰረት ሕይወታችን እንዲለወጥ ያስችለናል። የመንፈስን እሳት እንዳናዳፍን ሊረዱን ከሚችሉ አካሄዶች አንዱ “ትንቢትን አትናቁ” (1ተሰ. 5፡20) የሚለውን ምክር በተግባር ማዋል መቻላችን ነው። ጳውሎስ የተሰሎንቄ አማኞች ትንቢታዊ መልእክቶችን እንዳይንቁ ነገር ግን ፈትነው እንዲቀበሉ (1ተሰ. 5፡21) ትምህርት ሲሰጣቸው እናያለን። እንደ ቤተ ክርስቲያን አባልነታችን ራሳችንን ለትንቢታዊው መልእክት ክፍት ልናደርግና የመንፈስ ቅዱስ ሥራ እንዳይዳፈን ልንጥር ይገባል። በተጨማሪ የስህተት አስተምህሮዎችና ሐሰተኛ ነቢያት በቤተ ክርስቲያን ላይ እርግማናቸውን ማውረዳቸውን ስለማያቆሙ ማንነታቸውን መፈተንና መፈተሽ ከእኛ ይጠበቃል።

መንፈሶች ሁሉ ገር አይደሉም። በመንፈስ አነሳሽነት የተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ለእግራችን መብራት ለመንገዳችንም ብርሃን ነው (መዝ. 119፡105)። መጽሐፍ ቅዱስ አዳዲስ ትንቢታዊ መልእክቶችን ጭምር የምንመዝንበት አምላካዊ ቃል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈበት በኋለኛው ዘመን የምሽት መንገደኞችን እግሮች ከእንቅፋት የሚጠብቁ የኩራዝ መብራቶች ጥቅም ላይ ይውሉ ነበር። በመንፈስ እንዴት መመላለስ እንዳለብን (ገላ. 5፡25) መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል። ይህን ማድረግ የምንችለው ራሳችንን ለአምላካዊው ቃል አስተምህሮ አሳልፈን በመስጠትና እንዴት መኖር እንዳለብን የሚያመላክተንን--በልባችን ውስጥ መነሳሳት የሚፈጥረውን መንፈስ ቅዱስ ስንታዘዝ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስን እንደ እግዚአብሔር ቃል አድርገው ማመናቸውን የሚናገሩ ብዙዎች--ብርቱ ሥልጣን ያላቸውን መልእክቶች ትርጉም ዐልባ ፍቺ በመስጠት ቃላቶቹ በሕይወታቸው ሊኖሯቸው ይችል የነበረውን ኃይል ይሰርቃሉ። በተጨማሪ የእግዚአብሔርን ቃል ዝቅ አድርገን ስንመለከትና ለመልእክቱ መስጠት ያለብንን ክብር ስንነፍግ ወይም ደግሞ እንደ ቃሉ መመላለስን ቸል ስንል--ለመንገዳችን ብርሃን እንዲሆነን የተሰጠንን መብራት በማጥፋት ህሊናችንን ከመልካሙ ተግባር እናሰናክለዋለን።

ይህን ጥቅስ ያንብቡ፡-- 1ተሰ. 4፡7-8። “በቅድስና” እንድንመላለስ መጠራት ምን ማለት ነው? በእርግጥ “በቅድስና” እየተመላለሱ ስለ መሆንዎ ሊፈትሹአቸው የሚገቡ የሕይወትዎ ክፍሎች ይኖሩ ይሆን?

*ሐሙስ መጋቢት 7* *Mar 16*

### *መንፈስ ቅዱስን መሳደብ*

**ጥቅሶቹን ያንብቡ፡-- ማር. 3:28- 29፣ ሉቃ. 12:10፣ ማቴ. 12:31- 32። ማንኛውም ኃጢትም ሆነ ስድብ ይቅር መባል የሚችል ከሆነ ይቅር የማይባለው የትኛው ነው?**

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------

ምናልባት መንፈስ ቅዱስን ስለ መሳደብ የተነገረውን ያህል በክርስቲያኖች መሃል ታላቅ ጥርጣሬና ጭንቀት መፍጠር የቻለም ሆነ በስህተት የተስተዋለ ሌላ ኃጢአት የለም፡፡ አንዳንዶች--የሱስ ሌሎች የከፉ ኃጢአቶችን በአእምሮው እንደ ያዘ ነው ስለዚህ ኃጢአት የተናገረው በማለት ያስባሉ፡፡ ምንም እንኳ የአንዳንድ ኃጢአቶች ውጤት ከሌሎች በተለየ አስከፊ ቢሆንም ነገር ግን ሁሉም ኃጢአቶች በእግዚአብሔር ፊት አሰቃቂ መሆናቸውን በሚገባ እንገነዘባለን፡፡ የሆነው ሆኖ--ለመሆኑ የሱስ ይቅር ስለማይባለው ኃጢአት ሲናገር ምን ማለቱ ነበር?

እንደ እውነቱ ከሆነ ከእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ አንደኛውም ቢሆን ይህ ኃጢአት አይሰረይለትም ወይም ይቅር አይባልም እንጂ ይቅር መባል አይችልም አይልም፡፡ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ኃጢአተኞች ኃጢአታቸውን እንዲያስተውሉ ማድረግና ብቸኛውን ይቅር ባያቸውን የሱስን እንዲመኙ ልባቸውን መቀስቀስ ነው፡፡ ስለዚህ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚነገር የስድብ ቃል ሊስተዋል የሚገባው--የየሱስን አዳኝ ሥራ ሆነ ብሎ ያለማቋረጥ መቃወም፣ መካድ በሚለው ፍቺው ነው፡፡ አንድ ሰው በፈቃዱና በግትርነት--መንፈስ ስለ የሱስ የሚሰጠውን ምስክርነት፣ በየሱስ የሚያገኘውን ደኅንነትና ጸጋ ሲቃወም ይህ ገቢራዊ ይሆናል፡፡

የሱስ ከስም ማጥፋት ጋር ተያያዥነት ስላላቸው ጥቂት ቃላት እየተናገረ አይደለም፡፡ መንፈስ ቅዱስን መሳደብ--ባለማመን ጸንቶ በየሱስ ላይ ግልጽ ጥላቻ ማሳየት ከሚለው ዐውድ ጋር ብቻ የተያያዘ ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስን መሳደብ በአንድ ድርጊት ላይ ብቻ ተወስኖ የተቀመጠ ነገር ሳይሆን አንድ ሰው ቁርጥ ሃሳቡ አድርጎ የሚገፋበት የሕይወት መስመር ነው፡፡

“የተሰጣቸውን ተጨባጭ ማስረጃ በመቀበልና የክርስቶስ የጽድቅ ሥራ ውጤት ለሆነው ሰማያዊ ስጦታ እውቅና በመስጠት ፋንታ እርጉም ዓላማቸውን አጽንተው በመያዛቸው--ይህን አስገራሚ ታምራት ያደረገው በዲያብሎስ አማካይነት--ተባለ፡፡ ይህ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ኃጢአት መሥራት ነው፡፡”–Ellen G. White, Loma Linda Messages, p. 156.

ሰብዓዊው ልብ በእግዚአብሔር ላይ ግትር አቋሙን እንደ ያዘ በመጽናት የሱስን (አውቆ) ሲቃወም--እግዚአብሔር በየሱስ መሥዋዕትነት አማካኝነት ያስገኘለትን ደኅንነት ለመቀበል ስለሚደነድን የመንፈስ ቅዱስን ምስክርነት ከመቀበል ይሰናከላል፡፡ ይህ ኃጢአት ይቅርታ ሊያገኝ ከሚችልበት ቅጥር ውጪ የሆነው እግዚአብሔር ግለሰቡን ማዳን የሚችል ኃይል ስለሌለው ወይም ይቅር ለማለት ፈቃደኛ ባለመሆኑ አይደለም--ኃጢአተኛነቱን መገንዘብ የማይችል በመሆኑ እንጂ፡፡

በዚህ የተነሳ ግለሰቡ በየሱስ የሚገኘውን የኃጢአት ይቅርታ ለመቀበል አይችልም፡፡ እንዲህ ያለው አቋም ዘላለማዊ ውጤት እንዳለው እሙን ነው፡፡

እግዚአብሔርንና መንፈስ ቅዱስን በመቃወም እየኖርን ላለመሆናችን አጥብቀን ስለ ራሳችን ልንናገር ብንችልም ነገር ግን ይህ ላለመሆኑ እርግጠኞች መሆን የምንችለው እንዴት ነው? (1ዮሐ. 5:3፣ ሮሜ. 8:14.)

## ተጨማሪ ሃሳብ:-

ሰዎች ይቅር የማይባለውን ኃጢአት ሠርተው እንደሆን በብዙ መሸበር መጠየቃቸው በእርግጠኝነት ይህን ኃጢአት አለመሥራታቸውን ገልጦ ያሳያል። ይህን ኃጢአት ሠርተው ከሆነ ምንም የሚያሳስባቸው ነገር ሊኖር አይችልም። መሸበራቸውና መጨነቃቸው አሁንም እየመራቸው ላለው መንፈስ ክፍት ለመሆናቸው እርግጠኛ ማስረጃ ነው። ማንም ቢሆን የየሱስን ጽድቅ፣ ምግባርም ሆነ እሴት በእምነትና እርሱን በመታዘዝ የራሱ አድርጎ ሊወስድ የተገባ ነው። "የእግዚአብሔር ጽድቅ" (ሮሜ. 10:3) የሆነውን የክርስቶስ ጽድቅ በመልበስ ብቻ አሁን አጥብቀው ያጡት ሰላምና ደኅንነት ባለቤት መሆን ይችላሉ።

እግዚአብሔር በትክክል ይቅር ሊለው የማይችል አንድ ብቻ ሰው ያለ ሲሆን እርሱም የየሱስን ይቅርታ ላለመቀበል አብልጦ በግትር አቋሙ የጸናው ነው። "መንፈስ ቅዱስን የመሳደብ ኃጢአት ድንገት ከአንደበታችን አምልጦን የሚወጣ ቃል ወይም ድርጊት ሳይሆን--በአምላካዊው እውነትና ተጨባጭ ማስረጃ ላይ ልብን አደንድኖ ግትር አቋም መያዝ ነው።"–Ellen G. White Comments, The SDA Bible Commentary, vol. 5, p. 1093. በምስጢራዊውና እንዲህ ተብሎ በሰብዓዊ አእምሮ ሊገለጥ በማይችለው መንፈስ ቅዱስ ላይ ኃጢአት ለመሥራት የሚፈልግ ሊኖር አይችልም። ይልቁንም ወደ ንስሐ ለመምጣት አሻፈረኝ ብሎ በግትር እምቢታ መጽናት--በእርግጥም በመንፈስ ቅዱስ ለይ የሚሠራ ኃጢአት ነው።"–Page 1093.

## የመወያያ ጥያቄዎች

- አንድ ሰው ወደ እርስዎ መጥቶ ይቅር የማይባለውን ኃጢአት እንደሠራ የሚሰማው መሆኑን ቢነግሮት ምን ይመልሱለታል? የትኞቹን ጥቅሶች ተጠቅመው ሊረዱት ይሞክራሉ? እንደ ጠፋ ለሚሰማው ተስፋ የቆረጠ ሰው የደኅንነት በእምነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ብቻ ፍቱን ሊሆንለት የሚችለው ለምንድን ነው?
- የመንፈስ ቅዱስን ምሪት በአንደበታችንም ሆነ በድርጊታችን ለመግለጥ ስንቃወም መንፈስን እናዳፍናለን። የመንፈስን እሳት የማዳፈን አደጋ የተጋረጠብን የት ላይ ነው? ማለትም--አምላካዊውን ምሪት ለመቋቋም የሚዳዳው የሕይወታችን ክፍል አለ? ራሳችንን ለመንፈስ ማስገዛትን መማር የምንችለው እንዴት ነው?
- አንዳንዴ እግዚአብሔር ወደ ሕይወታችን ለመምጣት ገቢራዊ እንዲሆኑ የሚፈቅዳቸው ክስተቶች--ማለትም እንደ ሐዘን ወይም ልናስተውለው የማንችለው ዓይነት አጋጣሚ ሊፈጠር ይችላል። ለአብነት ያህል የኢዮብን ታሪክ እናስታውስ። በሐዘን የተሰበረ ልብ ለመንፈስ ቅዱስ አሠራር ክፍት የሆነው ለምንድን ነው? በአስቸጋሪ ሁናቴም እንኳ ለእግዚአብሔር ሙሉ ለሙሉ ታማኝ የምንሆነውና ሕይወታችንን የምንሰጠው እንዴት ነው?
- አንዳንዶች በቤተ ክርስቲያን ያለው ተጽእኖ አጉል እንደሆነ ስለሚሰማቸውና በተጽእኖው "እንዳይበክሉ" ስለሚሰጉ ራሳቸውን ሙሉ ለሙሉ ከቤተ ክርስቲያን አካል ይነጥላሉ። ይህን ማድረግ ስህተቱ ምኑ ላይ ነው? ምሳሌው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነና አንድ ክርስቲያን ሊከተለው የማይገባ የሆነው ለምንድን ነው?